# ግምገማ

ሲራክ ከሚድ ዌስት - July 2010

ካመት አመት ስህተትን እየደጋገምን ላንባገነን ገዥዎች ሲሳይ መሆኑን የቀጠልን ይመስላል። በተለይ አትራፊ የፖለቲካ ድርጅቶች ቁጥር በየቀኑ እየጨመረ ባለበት በዚህ ጉድ ዘመን ከነዚህ አይነት ፀረ-ህዝብ አጭበርባሪ ድረጅቶች ጋር ተባብሮ ለውጥ ለማምጣት እየሞከርን የመታገል ጉልበታችንን እያመከን ያደናጋሪ ሃይሎችንና ያሰማራቸውን የወያኔን አቅም እየገነባን መሂዱ የግድ ማቆም አለበት። ይህን ፅሁፍ ለመጻፍ ያነሳሳኝ ምክንያት በቅርቡ በኢ.ሕ.አ.ፓ ለሃቀኛ ተቃዋሚ ድርጅቶች የቀረበው የትግል መስመርን የሚያመላክት ጠቃሚ ምክር ስላየሁ ነው። ይህ ድርጅት የትግል ልምዱን ማቅረቡ የሚያስመሰግነው ቢሆንም የሚጠበቅበትም ነው። በተለይም ሕዝቡ መሪ አታጋይ ድርጅት በሚሻበት ሰአት ኢ.ሕ.አ.ፓ ምላሽ መስጠቱ የሚያበረታታ ነው። ኢ.ሕ.አ.ፓም ስለ ቀጣዩ ትግል ዘዴ የሚያምንበት መሰረታዊ መስፈርቶችን በሚገባ አስምሮበት ታጋይ ድርጅቶችም መመሪያቸው እንዲያደርጉ በተመክሮ የዳበረውን ምክሩን ማሰማቱ የድላችንን ቀናት ያሳጥረዋል የሚል ጠንካራ እምነት አለኝ። ወደ ትምህርታዊው መልእክት ከመግባቴ በፊት ግን ስላሳለፍነው ትግል የግሌን ግምገማ ማድረግ እፈልጋለሁ። ግምገማዬ <u>ድክመቶቻችን፣ ጥንካሬያች፣</u> **ተስፋና ስጋት** የተባሉትን የግምገማ ዘዴዎችን በመጠቀም ይሆናል።

በሕዝባዊ አመጽ የፊውዳሉን ስርአት ዳግም ላያገግም ገረሰስነው። መጣሉን ቻልንበት ግን አመራር ለመስጠት ስልጣኑን በጃችን ለማቆየት ባለመቻላችን በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ ሰው በላ የሆነ የደርግ መንግስት ለአያሌ አመታት ፍዳችንን አስቆጠረን። እርሱም በተራው በሕዝባዊ አመጽ ተንኮታኩቶ ፈረጠጠ። መርገም ሆኖብን ዘረኛ አገር አፍራሽና ሕዝብን ከፋፋይ የሆነው ስመጥፉው ወያኔ በላያችን ላይ ቁጢጥ ብሎ ይህ ነው የማይባል ጥፋት እየፈጸመብን አለ። ወያኔም በተራው በሕዝብ አመጽ ድባቅ እንደሚመታ የተረጋገጠ ሃቅ ነው። የሁላችንም ስጋት ማነው ባለተራ የሚለው እንደሆነ ይረዳኛል። መቸም ለሶስተኛ ሞኝነት መዳረግ በፍጹም አይገባንም። ሁለቱም የጥፋት መንግስቶች የገዙን ሕዝቡን የሚመራ ጠንካራ የፓለቲካ ድርጅት ባለመኖሩ ብቻ ይመስለኛል መልሱ። ጠንካራ ድርጅትም እንዳይመራ ብሎም እንዳይኖር ከወያኔ በበለጠ የሚደክሙ ድረጅቶችም መኖራቸው ያደባባይ ሚስጢር ሆኗል። እነዚህ ድርጅቶች ከወያኔ ከመታገል ይልቅ ቅድሚያ የሚሰጡት ኢ.ሕ.አ.ፓን መኮነን፣ ማጣጣልና የሌለ ወይም የጠፋ (ሲያልሙ-ይኑሩ እንጂ...) አድርጎ ማውራት ይቀናቸዋል። ፍላጎታቸው ግልጽ ነው። በዚህኛው ባላ ላይ ሆነህ ተቃዋሚ ምሰል። ተቃዋሚው ካሸነፈ እኔ ነኝ ነጻ ያወጣሁህ ጡሩምባ ሊነፋ ሲሆን ካላሸነፈም ደግሞ የወያኔ ወዳጅ መስሎ ለመቅረብ ነው።

የዚህ ጽሁፍ መሰረታዊ አላማው አንድና አንድ ብቻ ነው። የተሳሳትነውን ለማረም ጥሩ የሆንበትን ደግሞ ወርሰን ለወደፊቱ ትግል ለማስተላለፍ ነው። ትግሉን በሚገባ ለመምራት ወይም በትግሉ ለመሳተፍ በቅድሚያ ራሳችንን መመርመር የግድ ይሆንብናል። ሁላችንም ስህተታችንን፣ ድክመታችንን፣ ጥንካሬያችንን ደግሞም ተስፋችንን በመገምገም አስተዋጽኦ እንድናደርግ ልጋብዛችሁ። የኔ ግን ይሄው እንደሚከተለው።

## በመጀመሪያ በጥንካሬአችን ልጀምር፡-

- ከጸሃይ በታች በምድረ ኢትዮጵያ የሕዝቡን ሃይል የሚሊቅ አንዳችም ነገር የለም። ሕዝባችን የተከማቸ ሃይል ያለው ከመሆኑም ባሻገር ወያኔ አጥፊ ጠላቱ እንደሆነ ገና ከጅምሩ ተገልጸለታል። ስለወያኔ መጥፎነት ቅስቀሳ በማድረግ የሚባክን ጊዜ የለም። ቅስቀሳ በራሱ ጊዜ የሚወስድ ብቻ ሳይሆን ገንዘብም ዕውቀትም ጉልበት የሚፈጅና ቀስቃሽ ሃይልን አስልጥኖ ማውጣት ይጠይቃል። ይህ ሁሉ መሟላቱ ጥንካሬአችን ሆኖ ይቆጠራል።

- ሌላው ጥንካሬያችን ደግሞ በተመክሮ የበለጸገ ወያኔን ገልቦ በሚገባ የሚያውቀው ኢሕአፓ ዛሬም ልክ እንደ ትናንትናው በግንባር ቀደምትነት መስዋእትነትን እየከፈለ መሆን የሚገባውን የትግል መንገድ እያመላከተ ይገኛል። አመራር መስጠት ማለት ይህ ነው። ልናነግበው የሚገባን አንዱ ጥንካሬያችን ነው።

- እንዲሁም ደግሞ በገንዘብ ተገቢውን እርዳታ ሊያደርጉ የሚችሉ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆቸዋ በዲያስፖራው ውስጥ እንዳሉ በተደጋጋሚ ጊዜ የታየ ሃቅ በመሆኑ ተጨማሪ ጥንካሬያችን ነው።

- ይህ አገር ወዳድ ሕዝብ ቁርና ሃሩሩን ሳይፈራ የኢትዮጵያ ሕዝብን ሰቆቃ ገሃድ ለማድረግ ከፍተኛ የዲፕሎማሳዊና የማጋለጥ ብሎም በገገርው መንግስት ላይ መአቀብ እንዲጫንበት የሚጠሩ አያሌ ዲፕሎማቲካዊ ትግሎችን የማከናወን ችሎታ ያለው ሰፊ ህዝብ በውጭ አገር አለ።

- ሌላው ጥንካሬ ሆኖ መጠቀስ የሚገባው ደግሞ ቴክኖሎጂው የፈቀደልንን የግኑኝነት ዘዴዎችን ማለትም - ቴሌ ኮንፍረንሰ፡ ፓልቶክ፡ ኢንተር ኔት፡ ኢሜል፡ ራዲዮ … በስፋትና በፍጥነት የመጠቀም እድሉና አቅሙም መኖሩ ሌላ ጥንካሬያችን ነው።

- ከማንኛውም በላይ ደግሞ ዛሬ የትግሉ መንገድ ከመስታወት በላይ ጠርቷል። ሕዝባችን ከመቼውም ጊዜ በላይ መሪ ድርጅቱን ሰይሟል። ይህ ድርጅት ደግሞ ኢሕአፓ ነው። ይህ ደግሞ ድርጅቶች በሙሉ በኢሕአፓ ስር ይሁኑ ለማለት

ሳይሆን ግን የትግሉን ጎዳና ከሱ ይማሩ ለማለት ነው። ድርጅቱ ኢ.ሕአፓ አንዴም ጸረ ሕዝብ አቋም ወስዶም አያውቅምና።

## ድክመታችን፡-

- ✓ የመጀመሪያው ድክመታችን ከላይ የጠቀስኳቸውን ጥንካሬዎቻችን በተገቢው መንገድ መጠቀም ያለመቻላችን ነው።

- ✓ ሌላው ደግሞ ወዳጅ የሚሆነውን ጠላት፣ ጠላትን ደግሞ ወዳጅ አድርጎ መረዳቱ ነው። ወያኔን ትቶ በኢ.ሕአፓ ላይ የሚዘምተው የፓለቲካ ድርጅትና ፓለቲከኛ ማስተዋሉ በቂ ምሳሌ ነው። ወያኔን ለማጥፋት ደግሞ ሻዕቢያን መጠቀም የሚል ቅዠት ማመን፣

- ✓ ትክክለኛውን የትግል ዘዴ አለማወቁም የበለጠ ድክመታችን ሆኖ ይገኛል። የያዝኩትን መንግስት የምትፈልጉ ከሆን ሜዳውም ፈረሱም ይሄው ብሎናል እኮ ወያኔ። ሰላማዊ ትግል በሚሰራበት ቦታና ሁኔታ ሁሉ ውጤት እንደሚያስመዘግብ የታወቀ ሲሆን፣ ያ ቦታና ሁኔታ ግን በወያኔ በተያዘችው ኢ.ትዮጵያ ውስጥ አለመሆኑን ያለመረዳት ችግር ተደጋግሞ ታይቷል። ወያኔን መጣል የሚቻለው ባመጽ ነው ማለት ጠመንጃ ማንሳት ብቻ የሚመስሏቸው ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። መታገል ያለብን በሁለ-ገብ የትግል ስልት መሆኑን ያልተገነዘቡ የተቃዋሚ ድርጅቶች ቁጥር መበርከቱ የትግሉን ጎራ አጣቦና መንገዱንም አጣሞ ይገኛል።

- ✓ የሕዝቡን ለጋስነት ያስተዋሉ ጮሌዎች ይህን ያህል ዶላር ከከፈልክ ያባልነት ምስክር ወረቀት እንሰጥሃለን፡ የትጥቅ ትግልም እንጀምራለን ብለው ባዶ ተስፋ ሲመግቡን ቆይተዋል። ባመታት ሳይሆን በጥቂት ወራት ውስጥ ወያኔን ልንጥለው ነው ተብለንም ነበር። በፖለቲካ አለም ዋሽቶ የሕዝብን ድጋፍ ለማግኘት ሲሞክር ቢታይም እንዲህ አይንት ማጭበርበር፣ ሕዝብን አዘናግቶ ዋሾውን ድርጅትና መሪዎቹን ከባህር እንደወጣ አሳ ነው የሚያደርጋችው። የትጥቅ ትግል ለማድረግ የውጭ አገር በተለይም ድንበር ነክ አገር ጋር አጋርነት መፍጠሩ የሚደገፍ ቢሆንም አጋር የሚሆነውን አገር በቅጡ መረዳት አጣብቂኝ ውስጥ ከመግባት ያድናል። የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው የሚለው መላ አጥፊ ሊሆን እንደሚችል መጤንም ይገባዋል። የጠላቴ ጠላት የኔም ጠላት ሊሆን አይችልም ከሚል ተላላነት መመደብ አልፈልግም።

- ✓ ሌላው ድክመታችን ደግሞ ቅራኔን እያረቁ በመቻቻል ከመቀጠል ይልቅ ትንሿን ችግር ተራራ አሳክሎ፣ ድርጅትን ለማሽመድመድ አንጀኛ መሆን ተዘውትሯል።

በድረጅቶችም መካከል ያለመፈላለግ ኅልቶ ይታያል። የድሮዎቹ ኢሰፖዎችና ከወያኔ የተተፉት ባለዘመኑ ትግሉን ልመራ ባይ ወንጀለኞች የዘረፉትን ብር በመጠቀም የትግሉን ጎራ ሲያምሱት ይታያሉ። ይባስ ብለውም በመቶ ሺ የሚቆጠር ሕዝብ የፈጀውን ቀይ ሽብር እንዳልነበር ሊነግሩን ደፍረዋል። የሚፈልጉት ከወያኔ ጋር ያለውን ትግል ፈር ለማስቀየስ በመሆኑ ሙሉ ለሙሉ ባይሳካላችውም በመጠኑም ሳያዘናጉን አልቀረም። በዘንድሮው ምርጫ ማግስት ለመጪው አምስት አመት ማሸነፍ ይቻላል ብለው ዝግጅት የጀመሩም እንዳሉ ተሰምቷል።

- ✓ ሰሞኑን ደግሞ እያቆጠቆጠ ያለ አዲስ የፖለቲካ እድገት አሸታለሁ። ሃይማኖትን የተንተራሰ የፖለቲካ ድርጅት ሊወለድ ተረግዟል። ባይወለድም መታሰቡ ብቻ ከፋፋይነት አለው።

## ስጋት

- ✓ የአገርና የሕዝብ ጉዳይ ቀልድ አይደለም። ስላልሆነም ልዩ ትኩረት መሰጠት አለበት። "ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው" እንደተባለ ሁሉ አገር ሲጠፋ የለማ እየመሰለ ነው። ግብጽ ባህርዳርን ሊያለማ ተፈቀደለትና ቦታ ገዛ ሲባል ስጋት ተሰምቷል። ለምን ሌላ ስፍራ አልተሰጠውም? ሀረር፣ ጅማ፣ ትግራይ ….. ቦታ መመራት ስላልፈለገ ይሆን ወይስ ከመሰረታዊው አላማው መራቅ ስላልፈለገ ይሆን? ያሁኑ የሱማሌና የኤርትራ ጦርነት ስጋት ወደፊት ይቀርና፣ ኢትዮጵያ ስጋቷ የውሃ ጦርነት እንደሚሆን የፈረጠሙ የፖለቲካ አዋቂዎች ተናግረዋል። ተገቢውን ስለላ ለማከናወን ግብጾች በወያኔ ታግዘዋል። ይህ ስጋት ቅዠት ነው ተብሎ መገመት የለበትም። ግብጽ እያሳሳቀችን የማይቀረውን ጦርነት እያመቻቸ ነው።

- ✓ በሱማሌ ላይ በወያኔ ግፌት የተፈጠረው  ጥላቻ ለዘመናት ከሱማሌ ሕዝብ ጋር ሊያዋጋን ይችላል የሚል ስጋት አለ።  ምናልባትም አሁን በጦርነት ሊበቀሉን የሚያስችል ሃይልና ችሎታ ባይኖራቸውም በኦጋዴን ነጻ አውጭ ታከው ጥቃት እየፈጸሙብን ስለመሆኑ በርካታ ምልክቶች ይታያሉ። ሰኔና ሃምሌ ከገጠመላቸውም የኦጋዴንን ግዛት የኔ ነው ብላ ትወስድ ይሆናል።

- ✓ ወገኛው ወያኔም መሰረታዊ አላማውን ቀስቅሶ ትግራይን ለመቁረስ ማሰቡ አይቀሬ ጉዳይ ነው። ምኞቱን ለማደለብ ከምስኪኑ ጎንደርና ወሎ ለም መሬት ስቧል። ትግራይን ለማስገንጠል  ለኦጋዴን ለኦሮሞ ብሶት ፈንጅ ነው። ያለጊዜው ከፈነዳ ደግሞ የሚጎዳው ራሱን ነው። ወያኔን ጥለው ወዲያውኑ የሽግግር መንግስት አቋቁመው ወደፊትም ለሚፈጠሩ ጠባብ ድርጅቶች እገዛ በማድረግ የመገንጠል ህልሙን ሊያሟላ መሞከሩ የማየይቀር ፍርሃትና ስጋት ነው።

- ✓ የሕዝብ አመጽ ወያኔን እንደሚያንኮታኩተው  ማስረጃ ማቅረብ ያስቸግረኛል የሚል ስጋት ባይኖረኝም ተተኪው መንግስት ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ስለመሆኑ ግን መስጋቴ አይቀርም። ምክንያቱም አሁንም በፖለቲካ ቡድኖች ላይ የሚታየው ከስህተት ያለመማር በሽታ ጎልቶ ነው ያለው።

## ተስፋ

- ✓ ድካማችን ማረም ከቻልን ባገራችንና በሕዝባች ላይ ይመጣል ብለን የምንሰጋው አደገኛ  ጉዳይ ሊቃለል ይችላል የሚል ብርቱ  እምነት አለኝ። ሕዝቡ ባስመሳይ ድርጅቶች ላይ ይህ ነው የማይባል ጠንካራ ውሳኔ ላይ ደርሷል።  የድርጅት ስምና ንብረት የሰረቁትን አንጃዎችም መሳቂያ አድርጓቸዋል። በሰፈሩት ቁና ሆነና እነሱም  ከሁለት በላይ ተሰነጣጥቀዋል። ሊሞቱ አንድ ሃሙስ ብቻ ስለቀራቸው ከእንግዲህ ህዝቡን ማመስ አይቻላቸውም።

- ✓ በወያኔ ብር የደለቡ አስመሳዮችም ፖለቲካ በቃኝ ማለት ጀምረዋል። ብር  ብቻ አምጡ የሚሉትም ረገብ ያሉ መስለዋል። ባይሉም የሚሰማቸው የለም፡፡ የመገንጠል እብደት ላይ ያሉትም ለምን ከኤርትራ አንማርም ማለት ይዘዋል። የኦሮሞ፣ የኦጋዴንና የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያ ወይም ሞትን መርጧል። ሌት ተቀን የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ የሚነዙበት ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብም ጆሮ ነፍጓቸዋል። ይህ ታላቅ ተስፋ ነው።

- ✓ ሲፈጠር ጀምሮ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን አለኝታዋ የሆነው ኢሕአፓ ዛሬም አቅሙ በፈቀደለት መጠን መስዋእትነትን በመክፈል አንድ  ኢትዮጵያ፣ አንድ ሕዝብ በማለት ለትግሉ አመራር እየሰጠ  መገኘቱ ተሰፋችንን ያጎለብተዋል። ሕዝቡም ተስፋው በዚህ ድርጅት ላይ ስለመሆኑ ማስተዋል አያስቸግርም። እንደ ኢሕአፓ አይነት ብርቱ ድረጅቶች ባይበዙም እንዳሉ እገምታለሁ።

- ✓ በተለይ አሁን አንደኛ አመቱን ያከበረው የወደፊት መሪ የሆነ ድርጅት በኢሕአፓ ስር ተዋቅሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋና አለኝታ የሆነው የወጣት ክንፍ አለሁላችሁ ማለቱ እጅግ በጣም ተስፋ ሰጭ ነው።

- ✓ ከደርግ ኢሰፓና ከወያኔ የተተፉ የጉድ ድረጅት ፈጣሪዊችም እንደ አቻምናው ጸረ-ኢሕአፓ ሩጫቸው ላይ ቀጥል ዘመቻቸው ተቀጭቷል። እንደ ትናንትናው ዛሬ ለኛ

70÷ ለናንተ 30÷ እንከፋፈል የሚሉ ንዋይ አሳዳጆችን የሀፍረት ጨርቅ እንዲለብሱ አድርጓቸዋል። ሕዝባችን ለነዚህ ወገበሰባራ ድርጅቶችና መሪ ነን ባዮች ስፍራ ላለመስጠት ወስኗል። ይህ ደግሞ ከፍተኛ ተስፋ ሰጭ ነው። ዳግም የገደሉንን መሪ አድርገን እንዳናስቀምጥ ሕዝባችን መመሪያ ሰጥቶናል። በመሆኑም ነገ ደግሞ መለስ ከወያኔ ቢተፋ ወይም ኢሳያስ ከሻዕቢያ ቢባረር የተቃዋሚ መሪ አድርገን ላለማስቀመጥ ሕዝባችን የሰጠንን ትእዛዝ ሳናወላዳ ማክበር ግዴታ አለብን ወደድንም ጠላንም።

ግምገማዬን አጠቃልያለሁ። ግን ከኢሕአፓ የተሰጠውን የትግል ፈር ጥቆማ ደግሜ ማስተጋባት የሚገባኝ ብቻ ሳይሆን ግዴታዬም በመሆኑ ቃል በቃል ላስቀምጠው ይፈቀድልኝ።

- የሃይሎች አሰላለፍ ማካተት የሚገባው የኢትዮጵያን አንድነት ያነገቡ አገር ወዳዶችና ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች እንደሆኑ ማረጋገጥ፣
- ወያኔን ማስወገድ የቅድሚያ የትግል ግባቸው ያደረጉ ሃይሎች ጎራ መሆኑ የታመነበት፣
- በጋራ የትግል ስልትና እቅድ/ግብ የሚስማሙ ወገኖች መሆን እንደሚገባቸው፣
- በብሄራዊ አርነት ትግል ብቻ ሳይሆን ለሃገራዊ ነጻነት፡ ለዜጎቿ፡ ለእኩልነትና አንድነት፡ ለዲሞክራሲ ስርአት ማመናቸውን ያረጋገጡ፣

ከላይ የተጠቀሰው የኢሕአፓ የተመክሮ ምክር ካቀረብኩት ግምግማ ጋር የሚስማማና ለግምገማዬ መፍትሄ ሰጭ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ አምኜ ተቀብዬዋለሁ። ሌላውም እንዲቀበለው የግል ጥሪዬን አቀርባለሁ።

እንበርታ!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!